መሲሁ

ኤል ኤም አብደላህ

ማውጫ

አህመድ እና ሃምዲ 3

የእግዚአብሔር በግ 5

የእግዚአብሔር ቃል 7

የእግዚአብሔር መሥዋዕት 9

ኃጢአት 12

የአብርሃም ልጅ 15

እግዜብሔር አንድ ነው 18

እግዚአብሔር እና ሰው 22

አባሪ 27

አህመድ እና ሃምዲ

አህመድ በአንድ ቢሮ ውስጥ ተቀጥሮ ይሰራ ነበር። በስራው ብዙም ደስተኛ እንዳልሆነ መናገር ሙሉ በሙሉ እውነት ባይሆንም ከመምሪያ ኃላፊው ጋር ለመግባባት ግን አስቸጋሪ ሆኖበት ነበር። ስለዚህ የሙያ ብቃቱን ለማረጋገጥ ዕድሉን አላገኘም ነበር። መምሪያው ብዙ አስቸጋሪ ፕሮጀክት በተመደበለት ጊዜ እንኳን ኃላፊው ሁልጊዜ ሁሉንም የስራ ዋጋ ወይም ምስጋና መውሰድ በሚችልበት ደረጃ ላይ እንዳለ ያረጋግጥ ነበር።
አህመድ ከአንድ ጊዜ በላይ ስራ ስለመቀየር ቢያስብም የስራ ዕድሎች ያን ያህል ብሩህ ተስፋ ሰጪዎች አልነበሩም። በዚህ ምክኒያት ለጊዜውም ቢሆን እንኳን የተሻለ ነገር ለማግኘት አስቸጋሪ ሆኖበት ነበር። ከዚህ በተጨማሪም አሁን የሚያገኘው ደመወዝ ከአብዛኞቹ ካሉት ስራዎች በተወሰንስ ደረጃ ከፍ ያለ ስለነበር አህመድ እዛው በተቋሙ ውስጥ ቆየ። ለሚስቱ እና ለሶስት ልጆቹ የሚያስፈልገውን ለማቅረብ የሚያስችል በቂ ገንዘብ አስፈላጊ ነገር ነበር። አህመድ በልጆቹ በጣም ይኮራ ነበር በተለይም በዩኒቨርስቲ የምህንድስና ትምህርቱን በሚከታተለው በበኩር ልጁ በሀሰን።
ከዕለታት አንድ ቀን በስራ ላይ ያለውን ሁኔታ ወደ ተሻለ ነገር የቀየረ አንድ ነገር ሆነ። ሃምዲ የአህመድን ቢሮ ተቀላቀለ። ከአህመድ በዕድሜ በጥቂት ታናሹ የነበረው ሃምዲ ሁል ጊዜ ደስተኛ፣ ተግባቢ እና ለመወዳጀትም ለእርሱ ቀላል ነበር። በመጨረሻም አህመድ የስራ ቦታ ጓደኛ አገኘ። ምሳ አብረው መብላትና ምሽት ላይም መገናኘት ጀመሩ። ሃምዲም አግብቶ አራት ድንቅ ልጆችን ወልዷል፡ በሁለት ወንዶች እና በሁለት ሴቶች ልጆች እግዚአብሔር ባርኮታል። አህመድ እና ሃምዲ ጥሩ ጓደኛሞች ሆኑ ብዙ ጊዜ አንዳቸው የሌላኛው ቤት ይገናኙ ነበር። ቁጭ ብለው ሻይ እየጠጡ ማውራት ይወዱ ነበር። ስለማንኛውም ነገር እየተጨዋወቱ ሰዐቱ ፈጥኖ ያልፍ ነበር።

በመጀመሪያ ላይ በዋናነት በቢሮ ውስጥ ስለሚሰሩ ስራዎች ያወሩ ነበር ግን ጊዜው እያለፈ ሲሄድ በሕይወት ውስጥ ስለሚነሱት አንዳንድ አስፈላጊ ጥያቄዎች መወያየት ጀመሩ። አህመድም ሆነ ሃምዲ ሀይማኖታቸውን አጥባቂ ነበሩ ነገር ግን አንድ አይነት እምነት አልነበራቸውም። አህመድ ሙስሊም ነበር፡ የቅርብ ጓደኛው ሃምዲ ደግሞ መጽሃፍ ቅዱስን አዘውትሮ የሚያነብ የመሲሁ (አል መሲህ) ተከታይ ነበር።

አህመድን በጣም ያስገረመው ነገር ቢኖር: ሀምዲን ይበልጥ እያወቀው በሄደ ቁጥር እምነቱን እና ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን የጠበቀ ህይወት የበለጠ እያከበረ መምጣቱ ነበር። አህመድም ጓደኛው ከእግዚአብሔር ጋር የጠበቀ ግንኙነት እንዳለው ተገነዘበ። እርሱም እራሱ በፍፁም አጋጥሞት የማያወቀው ነገር ስለነበረ ይህን ለማወቅ ጉጉት እንዲያድርበት አደረገው። ሀምዲ ከእግዚአብሔር ጋር ያለው ሕይወት ከመሲሁ ጋር የተገናኘ መሆን አለበት ሲል አህመድ አሰበ። በተመሳሳይ መንገድ ባይሆንም እንኳን አህመድም በመሲሁ ያምን ነበር። ስለ የማሪያም ልጅ ስለ ኢየሱስ (አኢሳ ኢብን ማርያም) በቁርዓን የተጻፈውን ሁሉ ያምን ነበር እና ለመሲሁ ጥልቅ አክብሮት ነበረው። መሲሁ ከድንግል ማሪያም (ማሪያም አል-አትህራ) እንደተወለደ፡ በእግዚአብሔር ፈቃድ ብዙ ተአምራትን እንዳደረገ እና ወንጌልን (አል-ኢንጅል) ከእግዚአብሔር እንደተቀበለ ያውቅ ነበር። በተመሳሳይ ሁኔታ አህመድ ስለ መሲሁ ህይወት ጥቂቱን ብቻ እንደሚያውቅ ተገነዘበ፡ እናም በቁርአንም ውስጥም ሳይቀር ብዙ ስሞች ስለተሰጡት ስለዚህ ታላቅ ሐዋሪያ (ራሱል) የበለጠ ለማወቅ ፍላጎቱ ጨመረ።

አንድ ቀን አህመድ በማወቅ ጉጉት ተውጦ፡ የቅርብ ጓደኛውን ሀሚድን ስለ መሲሁ ለመጠየቅ በመጨረሻ ላይ ወሰነ። ይህ ውሳኔ ወደ ለብዙ አስደሳች ውይይቶች ምክኒያት ሆነ።

የእግዚአብሔር በግ

“እስቲ ስለ ማርያም ልጅ ስለ ኢየሱስ ንገረኝ በእውነት ስለ እርሱ የበለጠ ለማወቅ እፈልጋለሁ።” ሲል አህመድ በጉጉት ጠየቀ።

ሀምዲ ለአፍታ አሰበና “መሲሁ ወደ እዚህ አለም ለምን እንደመጣ ለማወቅ ከፈልግህ የመስዋዕትን ትርጉም መረዳት አለብህ” አለው። “መስዋዕት ስትል ምን ማለትህ ነው?” አለ። አህመድ በመደነቅ፡
ሃምዲ በመቀጠል፡ “የመስዋዕትን ትርጉም” በኢድ አል-አድሃ (የመስዋዕት በዐል) ማየት እንችላለን እግዚአብሔር አብርሃምን (ሰይደና ኢብራሂም) ልጁን እንዲሰዋ እንደጠየቀው ታውቃለህ። የአብርሀም ልጅ አላህ ለእርሱ ቤዛ (ፊዳ) አድርጎ መስዋዕት ባያቀርብ ኖሮ ምን ይሆን ነበር?” “እስማኤል ይሞት ነበር” አለ አህመድ። “የመስዋዕት ትርጉም ይህ ነው” “በሌላ ሰው ምትክ የሚሞት ሌላ ማለት ነው። ሲል ሀምዲ መለሰ። እግዚአብሄር በምትኩ የሚሰዋ በግ ላከ። እኔም ልክ እንደ አብርሃም ልጅ ነኝ። እኔ በሞት ታይል ስር ነኝ” አለ ሃምዲ።
“ምን ማለትህ ነው?” አለ አህመድ ትንሽ ግራ በመጋባት። ሃምዲ ጠንከር ባለ ቃል” (በቅዱስ መፅሐፍ) እንዲህ ተብሎ ተፅፏል፦

“የታጢአት ደመወዝ ሞት ነውና ” (1)

የታጢያቴ ደሞዝ ሞት ነው። እኔ ታጢያተኛ ነኝ። እውነት ነው ሌሎች ሰዎች እኔን እንደ ፅኑ ታይማኖተኛ ሰው አድርገው እንደሚያዩኝ እውነት ነው።
በየዕለቱ ወደ እግዚአብሔር እጸልያለሁ፡ መፅሐፉን አጠናለሁ፡ አገለግለዋለሁ። ግን በእግዚአብሔር ፊት ታጢያተኛ ነኝ። ከእግዚአብሔር በስተቀር ፍጹም የሆነ ሰው አለን? ሲል ሀምዲ ጠየቀ “ከአምላክ በስተቀር ማንም የለም” ሲል አህመድ መለሰ።” በእግዚአብሔር ፊት ሁላችንም ታጢያተኞች ነን አይደል?” ሲል ሃምዲ ጠየቀ።
አህመድ “አዎ ያ እውነት ነው” ሲል ተስማማ።
“ እኔም ከአብርሃም ልጅ ጋር በሞት ታይል ስር ነኝ። ግን ለታጢአቴ የሚቀርብ መስዋዕት የት አለ? እግዚአብሄር ስለ እኔ ቤዛ የሚሆን መስዋዕት አልላከልኝምን?” በማለት ሀምዲ ጠየቀ። አህመድ በእርግጥ ምን እንደሚል አያውቅም ነበር። ሀምዲ በመቀጠል ”መጥምቁ ዮሐንስ (ያህያ ኢብን ዛካርያ) በመሲሁ ዘመን ይኖር ነበር። መሲሁን ለመጀመሪያ ጊዜ ባየው ጊዜ እንዲህ አለ፦

“እነሆ የዓለምን ታጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ!” (2)

“መሲሁ የሰው በግ አልነበረም። ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጣ ነው። ከላይ የመጣ ነው። የእግዚአብሔር መንፈስ (ሩህ አላህ) ድንግል (ማሪያምን)) ሸፈናት። እርሷም ፀነሰች ወንድ ልጅም ወለደች። እንደምታውቀው እርሱ ‘የመሪያም ልጅ ኢሳ’ ‘የአላህ ቃል(ካሊማት አላህ)’ ‘እንዲሁም የአላህ መንፈስ (ሩህ አላህ)’ ተብሎ ተጠርቷል። ንፁህ ነበር። እርሱ የእግዚአብሔር በግ ሆኖ ከሰማይ መጣ። መሲሁ በእግዚአብሔር ፊት ፍጹም ህይወትን በመኖር የእግዚአብሔር በግ መሆኑን አረጋግጧል። ፍፁም

የእግዚአብሔር በግ ስለነበር ‘ታላቁን እግዚአብሄርን ይቅርታ እለምናለሁ (አስታህፋር ኣላህ- አልአዚም)’ ማለት ያሰፈለገበት ጊዜ ፍጹም አልነበረም። ይሁን እንጂ የአለምን ኃጢአት ለማስወገድ የእግዚአብሔር በግ ሆኖ ስለመጣ መስዋዕት መሆን ነበረበት። ይህም የሆነው በራሱ ፈቃድ ሕይወቱን ለሞት አሳልፎ በመስጠት ነው። ከሙታንም በመነሳት ሕያው ሆኖ ወደ ሰማይ አረገ። አንድ ቀንም ወደ እዚህ ዓለም በክብር ይመለሳል” አለ።

ሃምዲ ለትወሰነ ጊዜ ዝም አለ፡ አህመድን ተመለከተና “እኔ እንደ አብርሃም ልጅ በተመሳሳይ ሁኔታ በሞት ኃይል ስር ነኝ። ነገር ግን ስለኃጢአቴ የሚሆን መስዋዕት አሁን በንጹህ በእግዚአብሔር በግ በመሲሁ በኩል አለኝ። እግዚአብሄር ለኃጢአታችን ሁሉ ይቅርታን እና በገነት ውስጥ (በጃና) የዘለአለም ሕይወትን ይሰጠናል። አህመድ መሲሁ የአንተን ኃጢአት ጨምሮ የሰውን ሁሉ ኃጢአት ተሸክሟል።”
አህመድ እያሰበ ለረጅም ጊዜ በዝምታ ተቀመጠ። ከዚያም ”መሲሁ የዓለምን ሁሉ ኃጢአት ካስወገደ እንግዲህ እኔ መሞት አያስፈልገኝም።” በዚህ ሁኔታ እኔ የዘልአለም ሕይወት አለኝ” አለ።
“አህመድ “አለ ሀምዲ፡ “አሁን የልደት ቀንህ ነው እንበልና፡ መሲሁ ስጦታ ይዞልህ መጥቶ በርህን አንኳኳ። ‘አህመድ ስጦታ ልሰጥህ እፈልጋለሁ- ከዛሬ ጀምሮ ለኃጢአት ሁሉ ይቅርታን፡ የዘልአለም ህይወትን እና ከእግዚአብሔር ጋር ግላዊና ሕያው ግንኙነት እንዲኖርህ እፈልጋለሁ። ነገር ግን አንዳንድ ቅድመ ሁኔታዎች አሉ። እነሱም፡-ከኃጢአትህ መመለስ እና ኃጢአትህን መናዘዝ እና፡ በእኔ መስዋዕትነት አማካኝነት ይቅርታን መቀበል ይኖርብሃል። ስጦታውን ከተቀበልክ ያንተ ነው ካልተቀበልክ ግን የአንተ አይደለም።”
አህመድ ተቀምጦ ያሰላስል ነበር። ግራ ተጋብቶ ስለነበር ምን እንደሚል በትክክል አያውቅም ነበር።
ሀምዲ እንዲህ አለ፡ ”ይህ ወጣ ያለ ምሳሌ ነው ብለህ ታስብ ይሆናል” ነገር ግን የእግዚአብሔር አገልጋይ በመሲሁ በኩል ወደ እግዚአብሄር የሚወስደውን መንገድ በገለጸ ቁጥር፡ ሕያው እና ከሞት የተነሳው የማርያም ልጅ ኢየሱስ በእርግጥ በራችንን እያንኳኳ ነው ማለት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡-

“እነሆ በደጅ ቆሜ አንኳኳለሁ፤ ማንም ድምፄን ቢሰማ ደጁንም ቢከፍትልኝ፥ ወደ እርሱ እገባለሁ ከእርሱም ጋር እራት እበላለሁ እርሱም ከእኔ ጋር ይበላል።” (3)

ሀሚድ አክሎም፡ ለመሲሁ በሬን ከፍቼ ወደ ሕይወቴ መጋበዜ እና እንጀራን አብሬ በመቁረስ ከእኔ ጋር ሕብረት እንዲኖረው ማድረጌ እግዚአብሔር ለሁሉም ሊሰጥ የሚፈልገውን ስጦታ እንደ መቀበል ማለት ነው” አለ።

“ስለ መሲሁ የነገርከኝ ነገር ውስጤን በጣም እንደነካኝ እንድታውቅ እፈልጋለሁ ሀምዲ፡
ስለተወያየነው ነገር ለማሰብ ጊዜ ያስፈልገኛል፡ በሚቀጥለው ጊዜ ስንገናኝ ስለ መሲሁ ተጨማሪ መስማት እፈልጋለሁ።”
“አል-ሰላሙ አለይኩም” (ሰላም በአንተ ላይ ይሁን)
“አሌይኩም አልሰላም (ሰላም በአንተ ላይ ይሁን)

የእግዚአብሔር ቃል

"ባለፈው ጊዜ ስለ ማርያም ልጅ ስለ ኢየሱስ የነገርከኝ ብዙ እንዳስብ አድርጎኛል። ውይይታችንን ከመቀጠላችን በፊት ስለመሲሁ እንዲመለሱልኝ የምፈልጋቸው ብዙ ጥያቄዎች አሉኝ ቅር እንደማትሰኝ ተስፋ አደርጋለሁ ብሎ አህመድ ትንሽ አየተጠራጠረ መጠየቅ ጀመረ።"
"እባክህ ትችላለህ ቀጥል" ሲል መለሰ ሀምዲ፡ አህመድ ምን ማለት እንደፈለገ በከፊል እየተረዳ።

አህመድ አሁንም በጥንቃቄ ጥያቄውን ጀመረ" እኛ ሙስሊሞች በሰማያዊ መጽሐፍት ማለትም በአል-ታውራህ (በሙሴ ፔንታቱክ)፣ በአል-ዛቡር (በየዳዊት መዝሙር)፣ በአል-ኢንጅል (በየኢየሱስ ወንጌል) እና በቅዱስ ቁርአን እንደምናምን ታውቃለህ። እንዲሁም ከቁርአን በስተቀር ሁሉም መጽሐፍት በአይሁዶች እና በክርስቲያኖች እንደተበረዘ ተምሪያለሁ። ስለዚህ በዚያ ውስጥ የተጻፈውን ሁሉ ለማመን አትችልም። ስለዚህ አንተ የምታምነው መጽሐፍ ቅዱስ የተበረዘ (ሙሁራፍ)፣ የእውነት እና የውሸት ድብልቅ ነው።"

"አሁን የምትለውን የሚያረጋግጥ ታሪካዊ ማስረጃ ማቅረብ ትችላለህ?" ሲል ሀምዲ ጠየቀ።
አህመድ ለአፍታ ካሰበ በኋላ የገረመው ግን ይሄን መሰረተ ቢስ ውንጀላ እንጂ ፍጹም ስምቶ እንደማያውቅ ተገነዘበ።
ሀምዲ በመቀጠል፡ "ይህ የመፅሐፍ ቅዱስ ሆነ ተብሎ የተደረገ ብረዛ መቼ እንደተፈፀመ ወይም እንዴት ሊሳካ እንደቻለ ልትነግረኝ ትችላለህ?"
"አይ እኔ አልችልም" አለ አህመድ ትንሽ ደንገጥ በማለት። "ማንም እንደዚህ ላሉ መሰረታዊ ጥያቄዎች መልስ ሰጥቶኝ አያውቅም።"

ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሀምዲ "ቁርዓን ሊበላሽ ይችላል ብለህ ታስባለህ?"ሲል ጠየቀው። አስታግፈር አላህ (አላህን ይቅርታ እጠይቃለሁ) አለ አህመድ። "ይህ ፈጽሞ ሊሆን የማይቻል ነው። አማኞች ማንም ሰው እንዲያበላሸው ቀርቶ እንዲሞክርም ፈጽሞ አይፈቅዱም።"
ሀምዲ እንዲህ ሲል መለሰ "መጽሐፍ ቅዱስን በተለየ መንገድ የምናየው ለምን ይመስልሃል? እውነተኛ አማኞች የሆነ ሰው ቅዱሳት መጽሐፍትን እንዲቀይር እና የተበላሸ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲዘጋጅ ይፈቅዳሉ ብለህ እንዴት ልታስብ ቻልክ? ሰማይን እና ምድርን በፈጠረው፣ ሁሉን አዋቂ እና ሁሉን ቻይ በሆነው በእግዚአብሄር አምናለሁ። ቃሉን ለሰው ልጆች የሰጠ ቃሉን ከመበላሸት የመጠበቅ ኃይልም አለው።"

ሀምዲ አይኖቹን አህመድ ላይ ተክሎ "አህመድ ነገር ሁሉ የሚሆነው እንደ እግዚአብሄር ፈቃድ እንደሆነ ታምናለህ?" ሲል ጠየቀው።
"አዎ፡ አምናለሁ" ሲል አህመድ መለሰ።

ሀምዲ በመቀጠል "እግዚአብሔር በመጀመሪያ ቃሉን ለዓለም እንደሰጠ ከዚያ በኋላ ቃሉ እንዲበረዝ እንደሚፈቅደ በእርግጥ ታምናለህ ወይስ ሁሉን ቻይ የሆነው አምላክ ቃሉን ከመበረዝ ወይም ከመበላሸት የመጠበቅ ኃይል የለውም?"
"አዎ! እግዚአብሄር ቃሉን እንዳይበላሽ የማድረግ ኃይል አለው" ሲል አህመድ ተስማማ።
"አህመድ መጽሐፍ ቅዱስ አስደናቂ መጽሐፍ መሆኑን ታውቃለህ? የተጻፈው በግምት በ1400 ዓመታት ባለው ጊዜ ውስጥ ነው። በውስጡም አል-ተውራህ (ፔንታቱክ)፣ አል ዛቡር (መዝሙረ ዳዊት)፣ አል-ኢንጂል (ወንጌል) እና ሌሎች በእግዚአብሔር ሐዋርያት (ረሱል) እና ነቢያት (አንቢያ) የተጻፉ ብዙ መፃሕፍትን ይዟል።
መጽሐፍ ቅዱስ በሁለት ክፍሎች የተከፈለ ነው "ብሉይ ኪዳን፡ መሲሑ ከመወለዱ በፊት የነበረውን ጊዜ የሚሸፍነው እና መሲሑ ወደ ዓለም ከመምጣት ጋር የሚጀምረው አዲስ ኪዳን ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በሦስት የተለያዩ ቋንቋዎች የተፃፈ ነው።"
"እነዚህ ቋንቋዎች ምን ነበሩ?" አህመድ ተደነቀ።
ሃምዲም "በዕብራይስጥ፡ በአረማይክ እና በግሪክ ቋንቋ ነው የተፃፈው" ሲል መለሰ። እግዚአብሄር ቃሉን ሲሰጠን ብዙ የተለያዩ ሰዎችን ተጠቅሟል። አንዳንዶቹ ነገሥታት ወይም የሀገር መሪዎች፥ ሌሎች ደግሞ እረኞች ወይም ዓሣ አጥማጆች ነበሩ። መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ተዓምር ነው፥ እጅግ ረጅም ጊዜ እና በጽሁፉ ውስጥ የተሳተፉ ብዙ የተለያዩ ሰዎች ቢኖሩም፡ መጽሐፉ በሙሉ በአንድ ላይ ተጣምሮ አንድ ወጥ አስደናቂ መፅሐፍ ሆኗል። በመላው በመጽሐፍ ቅዱስ አንድ የጋራ የሆነ ጭብጥ (ፍሬ ሀሳብ) አለ፣ ያም ጭብጥ መሲሑ (አልመሲህ)" ነው አህመድ።

"እግዚአብሄር ስለ መሲሑ ለ 1,400 ዓመታት ያህል የተናገረው እውነት ሊሆን ይችላልን?" አለ አህመድ በመገረም።
"አህመድ" አለ ሀምዲ በፈገግታ፡ እግዚአብሄር ስለ መሲሑ በታሪክ ውስጥ ሁሉ እስከ አሁን ድረስ ተናግሯል።"አለ።
"በእርግጥ ይህ ሊሆን ይቻላል?" አለ አህመድ በጥርጣሬ ተሞልቶ።
"አዎ በእርግጥ ይቻላል፡ ምክኒያቱም ለእግዚአብሔር ሁሉም ነገር ይቻላል፡ ሲል ሀምዲ መለሰ፡" በሚቀጥለው ጊዜ ስንገናኝ ስለዚህ ነገር ማውራት እንችላለን።"
"እኔም በጉጉት እጠብቃለሁ" አለ አህመድ።"
"አል-ሰላሙ አለይኩም።"
"አሌይኩም አል-ሰላም"

የእግዚአብሔር መሥዋዕት

“አኔ በአውነቱ መሲሑ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሁሉ ያለ ዋናው ጭብጥ እንዴት መሆን እንደቻለ ለማወቅ ጓጉቻለሁ” አለ አህመድ። መሲሑ ኃጢአታችንን የተሸከመ የአግዜብሔር በግ እንደሆነ የተነጋገርነውን ታስታውሳለህ?“ ሲል ሀምዲ ጠየቀ።
”በእርግጥ አስታውሳለሁ፡“ አለ አህመድ “ይህን አንዴት ልረሳው እችላለሁ?”
“እግዚአብሔር በታሪክ ሁሉ የሰውን ልጅ እስከ ማሪያም ልጅ ኢየሱስ ድረስ ስለመሥዋዕት ሲያስተምር ቆይቷል” አለ ሀምዲ። “በምን ዓይነት መንገድ?“ ሲል አህመድ ጠየቀ። “በቃየል (ቃቢል) በአቤል (ሃቢል) ዘመን፡ በምድር ላይ ስንት ሰዎች ነበሩ?” ሲል ሀምዲ ጠየቀ።
አህመድ ለጥቂት ግዜ አሰበና “አራት ሰዎች ብቻ ነበሩ”፡- አዳም፣ ሔዋን (ሃዋ)፣ ቃየንና አቤል” ሲል መለሰ።
”አራት ሰዎች ብቻ” አለ ሀምዲ፥ ሆኖም እግዚአብሔርን በመሥዋዕት ማምለክ አስፈላጊ መሆኑን ተረድተው ነበር። ይህንን እንዴት ማወቅ ቻሉ?” ሲል ሀምዲ ጠየቀ ቀጥሎም “እምክኒያቱም ግዚአብሄር ቅዱስ እና ንጹሕ ስለሆነ ሰው ደግሞ ኃጢአተኛ በመሆኑ ለኃጢአቱ ቤዛ ያስፈልገዋል። ኖህ (ሰይደና ኖህ) እግዚአብሔርን በመስዋዕት አመለከ። አብርሃም (ሰይደና ኢብራሂም) እግዚአብሄርን በመስዋዕት አመለከ። ሙሴ (ሰይደና ሙሳ)፡ ዳዊት (ሰይደና ዳውድ) እና ሁሉም ሐዋሪያትና ነቢያትም እግዚአብሄርን በመስዋዕት አመለኩ።” ሀሚዲ አክሎ ”እኔም በተመሳሳይ መንገድ እንደ ሐዋሪያት እና ነቢያት እግዚአብሔርን አመልካለሁ።”
“አይ አሁንስ እየቀለድክ ነው። ለእግዚአብሔር ለመስዋዕት በግ ለመግዛት ወደ ገበያ አትወርድም” አለ አህመድ ፊቱ በፈገግታ ተሞልቶ።
ሀምዲ ”እርሱ በመሥዋዕቱ ጊዜ ኃጢአቴን በተሸከመ የእግዚአብሄር በግ በሆነው በመሲሑ በኩል እግዚአብሔርን አመልከዋለሁ” ሲል መለሰ። (በመጽሐፍ ቅዱስ) እንዲህ ተብሎ ተጽፏል፦

“አንድ እግዚአብሔር አለና፥ በእግዚአብሔርና በሰውም መካከል ያለው መካከለኛው ደግሞ አንድ አለ፥ እርሱም ሰው የሆነ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው፤ ራሱንም ለሁሉ ቤዛ ሰጠ” (1)

“አንድ አምላክ ብቻ አለ፥ በእግዚአብሔር እና በእኛ መካከልም አንድ አስታራቂ ብቻ አለ፡ እርሱም እራሱን ለሁሉም ቤዛ (ፊዳ) አድርጎ ያቀረበው መሲሁ ነው ለአንተም ጭምር፡ አህመድ። በታሪክ ውስጥ ሁሉ እስከ ዛሬ ድረስ፥ ሰዎች ሕያው እግዚአብሔርን በመሥዋዕት አመለኩ።”
”አሁን ምን ማለትህ እንደሆነ መረዳት የጀመርኩ ይመስለኛል፥ ቢሆንም ግን ሙሉውን ስዕል መረዳት እንድችል ትንሽ ተጨማሪ ማብራራያ መስጠት ያስፈልግሀል።” አለ አህመድ በትህትና።
ከጥቂት ደቃቃዎች በኋላ ሀምዲ እንዲህ ሲል መለሰ” እግዚአብሔር በታሪክ ውስጥ በተለይም በሙሴ በኩል በተውራ ውስጥ (ፔንታቱክ) የመስዋዕትን ትርጉም እና ዓላማ ገልጧል። መስዋዕት ለኃጢአት ቤዛ ስለመሆኑ የህጉ (አል-ሸሪአ) አጠቃላይ ትምሕርት በሚከተሉት የቅዱሳን መጻሐፍት ክፍል ውስጥ በግልፅ ተፅፏል ፦

“እንደ ሕጉም ከጥቂቶች በቀር ነገር ሁሉ በደም ይነጻል፥ ደምም ሳይፈስ ስርየት የለም።” (2)

“ግን ይህ ሁሉ ስለመሥዋዕት የተሰጠው ትምሕርት ከማርያም ልጅ ከኢየሱስ ጋር ምን ግነኙነት አለው?“ አለ አህመድ በመደነቅ።”
“መልካም” አለ ሀምዲ “ስለ መስዋዕትነት ትርጉም ከሚሰጠው ትምሕርት በተጓዳኝ ስለመሲሁ ብዙ ትንቢቶች ተነግረዋል። ከተነገሩት ትንቢቶች መካከል መሲሁ ወደ እዚህ ዓለም ሲመጣ ስለ ኃጢአታችን ቤዛ ሆኖ እንደሚሰዋ የሚገልፁ ብዙ ትንቢቶች ነበሩ።
ሀምዲ መጽሐፍ ቅዱሱን አንስቶ ከፈተ። ጥቅሱንም ለአህመድ እያሳየ ”ነቢዩ ኢሳያስ መሲሁ ከመምጣቱ ከ 700 አመታት ገደማ በፊት ስለ መሲሁ መሥዋዕትነት ምን ያህል በትክክል እንደፃፈ እራስህ ተመልከት” አለው፦

“በእውነት ደዌያችንን ተቀበለ ሕመማችንንም ተሸከሞአል፤ እኛ ግን እንደ ተመታ በእግዚአብሔርም እንደ ተቀሠፈ እንደ ተቸገረም ቈጠርነው።
እርሱ ግን ስለ መተላለፋችን ቈሰለ፥ ስለ በደላችንም ደቀቀ፤ የደኅንነታችንም ተግሣጽ በእርሱ ላይ ነበረ፥ በእርሱም ቍስል እኛ ተፈወስን።
እኛ ሁላችን እንደ በጎች ተቅበዝብዘን ጠፋን፤ ከእኛ እያንዳንዱ ወደ ገዛ መንገዱ አዘነበለ፤ እግዚአብሔርም የሁላችንን በደል በእርሱ ላይ አኖረ።
ተጨነቀ ተሣቀየም አፉንም አልከፈተም፤ ለመታረድ እንደሚነዳ ጠቦት፥ በሸላቶቹም ፊት ዝም እንደሚል በግ፥ እንዲሁ አፉን አልከፈተም።” (3)

አህመድ በትንቢታዊ ቃሉ ከልቡ በመነካት “ይህ የተፃፈው የማርያም ልጅ ኢየሱስ ከመወለዱ በመቶዎች ከሚቆጠሩ ዓመታት በፊት ነው የምትለው?” አለ።
“አዎ” አለ ሀምዲ። “እንደ ነቢያቱ አባባል መሲሑ ከነቢዩ ዳዊት (ናቢ ዳዉድ) ቤተሰብ መምጣት ነበረበት። ከመሲሁ አንድ ሺህ አመታት ገደማ በፊት የኖረው ዳዊት የወደፊቱ ልጁን የመሲሑን ስቅለት በትክክል ተንብይዋል። ስቅለት በዝግታ አስቃይቶ የመግደያ ዘዴ ነበር። ከጥቂት ጊዜ በኋላ የተሰቀለው ሰው አጥንቶች ይለያያሉ፡ በተጨማሪም በብርቱ የውሃ ጥም ይሰቃይ ነበር። ነብዩ ዳዊትም ስለእርሱ እንዲህ ሲል ጽፏል፦

“እንደ ውኃ ፈሰስሁ አጥንቶቼም ሁሉ ተለያዩ፤ ልቤ እንደ ሰም ሆነ፥ በአንጀቴም መካከል ቀለጠ።
ኃይሌ እንደ ገል ደረቀ፥ በጕሮሮዬም ምላሴ ተጣጋ፥ ወደ ሞትም አሸዋ አወረድኸኝ።
ብዙ ውሾች ከብበውኛልና፤ የክፉተኞች ጉባኤም ያዘኝ፤ እጆቼንና እግሮቼን ቸነከሩኝ።
አጥንቶቼ ሁሉ ተቈጠሩ፤ እነርሱም አዩኝ ተመለከቱኝም።
ልብሶቼን ለራሳቸው ተከፋፈሉ፥ በቀሚሴም ላይ ዕጣ ተጣጣሉ።” (4)

“ዳዊት ይህን የፃፈው በእርሱ ዘመን ስቅላት የመግደያ ዘዴ እንኳን አልነበረም ነበር። ግን ከብዙ ጊዜ በኋላ በሮማውያን ተጀምሮ በመሲሑ ዘመን ጥቅም ላይ ውሎ ነበር።”
“ታዲያ እነዚህ ሁሉ ትንቢቶች በማርያም ልጅ በኢየሱስ ላይ ተፈጽሟል እያልክ ነው?“ ሲል አህመድ ጠየቀ።

“አዎ እነዚህ ብቻ ሳይሆኑ ሌሎች የተፃፉ ብዙ ትንቢቶች ሁሉ በመሲሁ ላይ ተፈፅሚል” ሲል ሀምዲ መለሰ። “መሲሑ ሕይወቱን ቤዛ (ፊዳ) አድርጎ ለመስጠት እንደመጣ በተለያዩ አጋጣሚዎች እራሱ አረጋግጧል። ስለ ራሱም እንዲህ ብሏል፦

“እንዲሁም የሰው ልጅ ሊያገለግል ነፍሱንም ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ እንጂ እንዲያገለግሉት አልመጣም።” (5)

“አህመድ፡ እግዚአብሄር በመፅሐፍ ቅዱስ ለሰው ልጆች ኃጢአት ስለ መስዋዕትነት የተገለፀው ትምሕርት እንዴት በመሲሁ በኩል ሙሉ በሙሉ እንደተፈጸመ አሁን ገብቶሃል?” ሀምዲ አለ አህመድ “ከዚህ በፊት በፍፁም ሰምቼው አላውቅም። በጣም የሚያጓጓ ነው። ተጨማሪ የማሰቢያ ጊዜ ያስፈልገኛል። ግን አታስብ ከተጨማሪ ጥያቄዎች ጋር በቅርቡ እመለሳለሁ።
“እባክህ ይህን መጽሐፍ ቅዱስ እንደ ስጦታ ተቀበለኝ” አለ ሀምዲ። “ስለ መሲሑ ሕይወት፣ ስለ አስደናቂ ተአምራቶቹ እና ትምሕርቶቹ ማንበብ በምትችልበት በአዲስ ኪዳን ጀምር።” አለ ሀምዲ።
“አመሰግናለሁ” አለ አህመድ። “ስለ የመጽሐፉ ሰዎች (አህል አል-ኪታብ) ብዙ ሰምቼያለሁ፡ ነገር ግን ከዚህ በፊት መጽሐፉን እራሱን አንብቤው አላውቅም። በእውነት ስለ ማሪያም ልጅ ስለ ኢየሱስ ትምሕርት እና ተአምራት ለማንበብ በጣም ጓጉቻለሁ።”
“አል-ሳላሙ አለይኩም።”
“አለይኩም አል- ሰላም።”

ኃጢአት

“ሀምዲ” አለ አህመድ ትንሽ እያመነታ ጀመረ፡ “ለመጨረሻ ከተገናኘንበት ጊዜ ጀምሮ ስለ መሲሑ እና ህይወቱን ስለ ሰው ልጆች ኃጢአት ቤዛ አድርጎ እንዴት እንደሰጠ እያሰብኩ ነበር። ግን አንድ ማወቅ የምፈልገው ነገር አለ። ኃጢአት (አል-ካቲያ) ከየት መጣ? የሰው ልጅ ሁሉ ከኃጢአት ጋር ችግር ያለበት እንዴት ነው? ይህን ማስረዳት ትችላለህ?” ሲል አህመድ በቁም ነገር ጠየቀ።
“አዎ ይመስለኛል” ሲል ሃምዲ በትህትና መለሰ“ ነገር ግን ኃጢአት ከየት እንደመጣ ለመረዳት ወደ መጀመሪያው መመለስ አለብን። እግዚአብሄር ዓለምን እና የሰውን ልጅ ከፈጠረ በኋላ ሰውን በገነት (በጃና) ውስጥ እንዳስቀመጠው (በታውራ/ኦሪት) እናነባለን። በዚህ በገነት (በጃና) ውስጥ ሰው ሙሉ በሙሉ ንፁህ ነበር፡ ከእግዚአብሔርም ጋር ፍጹም በሆነ ግንኙነት ይኖር ነበር። ግን እንደምታውቀው በገነት ውስጥ የነበረውን ሕይወት የሚያጠፋ ነገር አጋጠመ። አህመድ ምን ሆነ?”
“ሰይጣን መጥቶ ሁሉን ነገር አበላሸው” አለ አህመድ።
“በትክክል!” ሲል ሀምዲ መለሰ። ”ሰው መልካምንና ክፉውን ከሚያስታውቀው ዛፍ እንዳይበላ አዳምን በከለከለው ጊዜ እግዚአብሔር እንዲህ አዳምን አለው፡-

“እግዚአብሔር አምላክም ሰውን እንዲህ ብሎ አዘዘው፡- ከገነት ዛፍ ሁሉ ትበላለህ፤
ነገር ግን መልካምንና ክፉን ከሚያስታውቀው ዛፍ አትብላ፤ ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህና።”
(ነ)

“ሰይጣን ግን በእባብ ተመስሎ አዳምንና ሔዋንን ፈተናቸው። እነርሱም ለእግዚአብሄር አልታዘዙም እና ፍሬውንም በሉ። ውጤቱም ለሰው ልጅ አስከፊ ነበር። ኃጢአት ወደ ሰው ልጅ ሕይወት ስለገባ ሁሉም ኃጢአተኛ ሆነ።”
“በእርግጥ ሁሉም ኃጢአተኛ ሆነ?“ ሲል አህመድ በጥርጣሬ ጠየቀ። “ይህንን ለመቀበል ያስቸግረኛል። እውነት ከሆነ ግን ሁሉም ሰው ኃጢአተኛ የሆነው በምን መንገድ ነው?”
”የሰው ልጅ ልክ እንደበላው ፍሬ ሆነ” አለ ሀምዲ። “እሱ እንግዳ የሆነ የመልካም እና የክፉ ድብልቅ ሆነ። አንዳንድ ጊዜ አንድ ሰው በጣም የከበረ እና መልካም የሆኑ ድርጊቶችን ሊፈፅም ይችላል፡ ወዲያውኑ በቅጽበት በአንዳንድ መጥፎና አስከፊ የክህደት ድርጊቶች ሊሳተፍ ይችላል፡ ምናልባትም የገዛ ባልንጀራውን በማታለል እና በማጭበርበር ድርጊቶች ላይ ሊገኝ ይችላል። አንድ ሰው በአንድ ደቂቃ በጣም አፍቃሪ እና ለሰው አሳቢ ሊሆን ይችላል፡ በሚቀጥለው ደቂቃ በቅናት፣ በራስ ወዳድነት፣ በፍትወት ወይም ከኃጢአት ጋር በተያያዙ ሌሎች ባህሪያት ሊሞላ ይችላል። አህመድ አንተ እንዳልከው የሰው ዘር ሁሉ ከዚህ ችግር ጋር ይታገላል። እያንዳንዱ ሃይማኖት ይህን ችግር ለመፍታት ይጥራል። እያንዳንዱ ሀገር ኃጢአትን በተለያየ መልኩ ለመቆጣጠር ህጎችን ይደነግጋሉ። አስከፊው ነገር ግን ሰዎች ኃጢአትን ስለሚሰሩ ኃጢአኞች አለመሆናቸው ነው፤ ነገር ግን ኃጢአትን የሚሰሩት ኃጢአተኞች ስለሆኑ ነው። በሰዎች ውስጥ ኃጢአትን እና ክፋትን የሚያመነጭ ትንሽ ፋብሪካ እንዳለ ነው አይደል?“ አለ ሀምዲ አህመድን አተኩሮ እያየ።
”ይቅርታ ይሄ ስለ ሰው ልጅ የሰጠኸው ማብራሪያ ካለው ከእውነታው ጋር በጥሩ ሁኔታ የሚስማማ ነው። በእርግጥም ሰዎች የመልካም እና የክፉ እንግዳ ስራ ድብልቅ ናቸው።” ሲል መለሰ አህመድ።

“በዚህ ስዕል ውስጥ የሰይጣን ትክክለኛ ስፍራ የት ነው?”
“መልካም፡ ሰይጣን በሰዎች ሕይወት እና በህብረተሰቡ ውስጥ ስልጣን ያገኘው በኃጢአት ምክኒያት ነበር” ሲል ሀምዲ መለሰ።
“በአንድ ወቅት አዳምን እና ሔዋንን የፈተነ ዛሬም ተመሳሳይ ነገር እያደረገ ነው። አሁንም ሰዎችን በኃጢአት እየኖርን እንድንቀጥል ይፈትነናል። ከእግዚአብሔር የለየን ኃጢአት በመሆኑ፡ ዛሬም ሰይጣን በኃጢአት አማካኝነት በሰዎች ህይወት ውስጥ ኃይል ማግኘት ይችላል። ዛሬ በዓለም የምናየው ሁሉ የሆነው በኃጢአት ምክኒያት ነው። እግዚአብሄር ሁሉንም መልካም አድርጎ ፈጠረ፡ ነገር ግን የሰው ልጅ ብዙ ክፉ ነገሮችን ወደ ዓለም አምጥቷል፡ ለምሳሌ በጦርነት፣ በጭቆና፣ እንዲሁም በተበላሸ ግንኙነት እና የሰዎችን ሕይወት በሚያበላሹ በብዙ የመከራ ዓይነቶች የሰው ልጆችን ሕይወት አጥፍቷል።” እንግዲህ እግዚአብሄር እንዲህ አድርጎ አልነበረም የፈጠረን፡ ይልቁንስ በአዳም ኃጢአት የተነሳ ዓለማችን እንዲህ ሆነች እያልክ ነው?” አለ አህመድ በመገረም። “በትክክል!” ሲል ሀምዲ መለሰ። “በአዳም በኩል ኃጢአት ወደ ሰው ሁሉ እንደገባ እንዲህ ተጽፏል፦

“ስለዚህ ምክንያት ኃጢአት በአንድ ሰው ወደ ዓለም ገባ በኃጢአትም ሞት፥ እንደዚሁም ሁሉ ኃጢአትን ስላደረጉ ሞት ለሰው ሁሉ ደረሰ፤” (2)

“ከሁሉም የከፋው ውጤት ሞት ነው አካላዊ እና መንፈሳዊ ሞት ነበር።”
“አካላዊ እና መንፈሳዊ ሞት?” አለ አህመድ በጥያቄ ወደ ሀምዲ እየተመለከተ።
“መንፈሳዊ ሞት በትክክል ምንድን ነው?”
“ጥሩ፡ እግዚአብሄር ሰውን አትብላ ካለው ፍሬ ከበላ በእርግጠኝነት እንደሚሞት ነግሮታል” በማለት ሀምዲ ጀመረ። “እግዚአብሄርም ጻድቅ ስለሆነ እና ሁልጊዜም እንደ ቃሉ ስለሚሰራ ሰዎች ይሞቱ ዘንድ ሞት በሰው ልጆች ሁሉ ላይ መጣ። እንዲሁም ሰው ኃጢአት ሲሰራ በመንፈሳዊ መንገድም ሞቷል።”
“እንዴት?” አለ አህመድ እየተደነቀ።
“መልካም፡ የኃጢአት ውጤት ሰው ከገነት መባረሩ ነበር” በማለት ሀምዲ መለሰ።” ከእግዚአብሔር ጋር በንጹህና ፍጹም ግንኙነት ሲኖር ከነበረበት ቦታ ተባረረ። ሰው ከገነት ውጪ መኖር ነበረበት። ሰው በኃጢአቱ ምክኒያት ከሕያው እና ከቅዱስ አምላክ እንደተለየ መንፈሳዊ ሞትን ሞተ። ስለዚህ የሰው ልጆችን ከእግዚአብሔር የሚለየው ኃጢአት እና ክፋት ነው። ከእግዚአብሔር ጋር ቅፅበታዊ ግንኙነት መመስረት የማንችለው በኃጢአት ምክኒያት ነው። እግዚአብሄር ንጹህ እና ቅዱስ ስለሆነ ከኃጢአት ጋር ምንም ግንኙነት ሊኖረው አይችልም። ለዚህም ነው በኃጢአታችን ምክኒያት ከሚደርስብን መከራ የሚያድነን አዳኝ (ሙናጂ) ያስፈለገን። አህመድ፡ ኃጢአትህ ሁሉ በሆነ ቦታ እንደሚመዘገቡ ታምናለህ?”
“አህመድ ትንሽ እንደማዘን ብሎ “እያንዳንዳችንን በሚከታተሉ ሁለት መላዕክት እንደተመዘገቡ አውቃለሁ” አለ።
“እግዚአብሔር ስለ እኛ ሁሉንም ነገር ያውቃል” አለ ሀምዲ።” መልካም እና ክፉ ስራችን፣ እያንዳንዱ ቃል፣ እያንዳንዱ ሀሳብ፣ እያንዳንዱ ዓላማ (ኒያ) ሁሉም ነገር በእግዚአብሔር ተመዝግቧል። በፍርድ ቀን (ዮም አል-ሂሳብ) ሚዛኖች ወዴት እንደሚያዘነብል ታውቃለህ?
”አይ ይህን የሚያውቀው እግዚአብሔር ብቻ ነው” አለ አህመድ በቀስታ።
“እግዚአብሔር ይወድሃል አህመድ። የእግዚአብሔር በግ የማሪያም ልጅ ኢየሱስ” ኃጢአታችንን ሁሉ በራሱ ላይ ተሸክሞ እንዳስወገደ አትርሳ። ለሁሉም ነገር ይቅርታ ተዘጋጅቷል” አለ ሀምዲ በመረጋጋት።

አህመድ ለጥቂት ጊዜ አሰበና" መሲሑ ይሄን ያህል እጅግ አስፈላጊ ከሆነ አዳም እና ሔዋን ስለ እርሱ ለምን አልሰሙም" ሲል ጠየቀ።
"ስለ መሲሑ ሰምተው እንደነበር ብነግርህ ታምነኛለህ?"
ሲል ሀምዲ ጠየቀ "አይ! አዳምና ሔዋን ስለእርሱ ሊሰሙ የሚችሉ አይመስለኝም" ሲል አህመድ መለሰ።
"እግዜብሔር ሰውን ስለሚወድ ከእርሱ ጋር ግንኙነት እንዲኖረው ይፈልጋል" ሲል ሀምዲ ጀመረ። ለዚህም ነው ከመጀመሪያው ጀምሮ ስለ መሲሁ የተናገረው።" እግዚአብሔር ሰውን ይወዳል እናም ከእርሱ ጋር ግንኙነት እንዲኖረው ይፈልጋል"ሲል ሀምዲ ጀመረ። ለዚህም ነው ገና ከመጀመሪያው ጀምሮ ስለ መሲሑ የተናገረው። ይሁን እንጂ አዳም እና ሔዋን ዙሪያቸውን በተከበቡበት በአሳዛኝ ሁኔታ መካከል ሳሉ አንድ ቀን አዳኝ እንደሚያገኙ እና ሰይጣን በሰው ላይ ያለውን ኃይል እንደሚሰባብር ቃል ኪዳን ተቀበሉ። እግዚአብሔር አዳምና ሔዋን እየሰሙ ሰይጣንን እንዲህ ብሎ ተናግሮት ነበር:-

"በአንተና በሴቲቱ መካከል፥ በዘርህና በዘርዋም መካከል ጠላትነትን አደርጋለሁ፤ እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል፥ አንተም ሰኰናውን ትቀጠቅጣለህ።" (3)

"በመላው መጽሐፍ ቅዱስ ወንዶች ልጆች የሚጠሩት በአባቶቻቸው ስም ነው፡ የአብርሃም ልጅ፣ የያዕቆብ ልጅ እና ሌሎች የመሳሰሉት ወዘተ።
እዚህ ላይ ግን መጽሐፍ ቅዱስ የሚናገረው ስለ ሴቲቱ ዘር እንጂ ስለ ወንዱ ዘር አይደለም። አባት የሌለው አንድ ሰው ይልቁንስ የሴቲቱ ልጅ መምጣት ነበረበት። ይህ ልጅ በሰው ልጅ ላይ ያለውን የሰይጣንን ኃይል ያደቅቃል፡ ሰይጣን ደግሞ እንደ እባብ ተረከዙን በመንከስ የሴቲቱን ልጅ ለመግደል ይሞክራል። የማሪያም ልጅ ኢየሱስ ሕይወቱን ለሰው ልጆች ኃጢአት ቤዛ አድርጎ ሲሰጥ በትክክል የተከሰተው ይህ ነበር።"
"የሚገርም ነው" አለ አህመድ። "እግዚአብሔር ስለ መሲሁ በምድር ላይ ለመጀመሪያዎቹ ሰዎች ከጅምሩ መናገር መጀመሩ አስገራሚ ነው። ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ዋና ፍሬሀሳብ መሲሁ መሆኑን በድጋሚ ያሳያል። ለሚቀጥለው ጊዜ አስቀድሜ የማስብበትን ብዙ ነገር ሰጥተኸኛል ሀምዲ።"
"አል-ሰላሙ አሌይኩም"
"አሌይኩም አል-ሰላም"

የአብርሃም ልጅ

“እኔ በጣም ጓጉቻለሁ” “አንተ ስለ ወንጌል (አል-ኢንጅል) ምን እንደምታስብ ማወቅ እፈልጋለሁ።” አለ ሀምዲ። ”በእውነቱ አስደናቂ መፅሐፍ ነው፡” በማለት አህመድ በትሕትና መለሰ። “እንደዚህ ዓይነት በፍፁም አንብቤ አላውቅም።” መሲሁ ስለአደረጋቸው ድንቅ ተአምራቶች በዝርዝር ማንበብ ደስ የሚያሰኝ ነው። በተራራው ላይ ያስተማረውም ትምህርት (የተራራው ስብከት) እጅግ በጣም አስደናቂ ነው። የሚናገረው ሁሉ ግልጽ እና የጠለቀ ነው። ጠላቶቻችንን እንድንወድና ለሚያሳድዱን እንድንጸልይ ሲነግረን ብዙ ጽንሰ ሀሳቦችን የቀየረ ነው። ስለ ፀሎት የሚያስተምረው ትምህርትም ቢሆን ከዚህ በፊት ከሰማሁት ፍጹም የተለየ ነው። ይህ መጽሐፍ ጥልቅ ስሜትን እንደፈጠረብኝ መቀበል አለብኝ፡ የዚያኑ ያህል እንደመልሶቹ ሁሉ ብዙ አዳዲስ ጥያቄዎችንም ያጫረብኝ ይመስለኛል።” “ደስ ይላል” አለ ሀምዲ በፈገግታ።
“በመጀመሪያው ጥያቄህ እንጀምር።” እሺ አለ አህመድ “ለምንድነው ወንጌሉ ከአብርሃም እስከ ዳዊት እና መሲሑ ድረስ ባለው የዘር ሐረግ የጀመረው?” አለ።
ሀምዲ ለአፍታ ካሰላሰለ በኋላ፡ ”ከዚህ በፊት መጽሐፍ ቅዱስ አንድ የተያያዘ እና በመጽሐፉ ውስጥ ሁሉ የሚገኝ አንድ ጭብጥ (ፍሬ ነገር) እንዳለ የተነጋገርነውን ታስታውሳለህ?“ ሲል ጠየቀ። ”አዎ አስታውሳለሁ” ሲል አህመድ መለሰ። “ፍሬ ነገሩ (ጭብጡ) ምን እንደነበር ታስታውሳለህ? አህመድም “አል-መሲሕ” ሲል መለሰ። “የጥያቄህም መልሱ ከዚያ (ጭብጥ) ጋር የተያያዘ ነው” አለ ሀምዲ። “ነቢያቶች እንደተናገሩት መሲሑ የዳዊት ልጅ እና የአብርሃም ልጅ መሆን ነበረበት።”
አህመድ ሀምዲ የነገረውን ነገር አሰበና ”የተናገርከው ነገር ደስ የሚል ነው፡ ግን ስለ ተለያዩ ትንቢቶች ትንሽ ተጨማሪ ማብራሪያ መስጠት ትችላለህ?“ አለ።
ከብዙ ዝምታ በኋላ ሀምዲ እንዲህ በማለት ጀመረ” ከአራት ሺህ አመታት ገደማ በፊት፡ አንድ ቀን እግዚአብሔር የእግዚአብሔር ወዳጅ (ከሊል አላህ) በመባል የሚታወቀውን አብርሃምን አናገረው። አብርሃም ገና አብራም ተብሎ በሚጠራበት ጊዜ፡ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ሁሉ ታላቅ ትርጉም ያለውን የተስፋ ቃል ሰጠው። በኦሪት (በታውራህ) ውስጥ እንዲህ የሚል እናነባለን፡-

“እግዚአብሔርም አብራምን አለው፦ ከአገርህ ከዘመዶችህም ከአባትህም ቤት ተለይተህ እኔ ወደማሳይህ ምድር ውጣ።
ታላቅ ሕዝብም አደርግሃለሁ፥ እባርክሃለሁ፥ ስምህንም አከብረዋለሁ፤ ለበረከትም ሁን፤
የሚባርኩህንም እባርካለሁ፥ የሚረግሙህንም እረግማለሁ፤ የምድር ነገዶችም ሁሉ በአንተ ይባረካሉ።”
(ነ)

“እግዚአብሔር ለብዙ ዓመታት በትዳር ሆኖ ልጅ ያልነበረውን ሰው ጠራው። እግዚአብሔር ምድርን ተስፋ ሰጠው፣ ታላቅ ሕዝብ እንደሚሆን እና ስሙም ታላቅ እና ገናና እንደሚያደርገው ቃል ገብቶለት ነበር። እግዚአብሔር ተስፋውን ሁሉንም እያንዳንዱን በዝርዝር ፈፅሞታል። ነገር ግን ከሁሉም ተስፋዎች በላይ ከሁሉም አስደናቂው ጌታ እግዚአብሔር በምድር ያሉትን ሕዝቦች ሁሉ በአብርሃም በኩል መባረኩ ነው። በዚህ ተስፋ ውስጥ የመሲሑም ተስፋ አለ። ስለዚህ መሲሑ የአብርሃም ልጅ መሆን ነበረበት፥ በእርሱ አማካኝነት እግዚአብሔር አለምን ሁሉ ይባርካል።”

“ነገር ግን የተስፋው ቃል ስለ መሲሑ እንጂ ስለ ሌላ ሰው እንዳልሆነ እንዴት ታውቃለህ?” ሲል ጠየቀ አህመድ በመገረም።
“ታውራን (አሪትን) የበለጠ ስናነብ ቀስ በቀስ ግልጽ እየሆነ ይሄዳል ማለት እንችላለን” ሲል ሀምዲ መለሰ። ከጊዜ በኃላ አብርሃም ሁለት ወንዶችን ልጆችን ወለደ፡ አንደኛው ከሚስቱ ከሣራ የተወለደው ይስሃቅ የተባለው (ኢስሃቅ) ሲሆን፥ ሌላኛው ደግሞ ሃጋር (ሃጃር) ከተባለች ከሣራ አገልጋይ የተወለደው እስማኤልን (ኢስማኢሊን) ነው። እግዚአብሔር ይስሃቅ ከመወለዱ በፊት እስማኤልን ቢባርከውም፡ ስለ መሲሑ የገባውን የተስፋ ቃል ግን በይስሃቅ በኩል እንደሚፍጸም ለአብርሃም በግልፅ እንዲህ ብሎታል፡-

“እግዚአብሔርም አለ፦ በእውነት ሚስትህ ሣራ ወንድ ልጅን ትወልድልሃለች፥ ስሙንም ይስሐቅ ብለህ ትጠራዋለህ፤ ከእርሱ በኋላ ለዘሩ የዘላለም ቃል ኪዳን እንዲሆን ቃል ኪዳኔን ከእርሱ ጋር አቆማለሁ። ስለ እስማኤልም ሰምቼሃለሁ፤ እነሆ ባርኬዋለሁ፥ ፍሬያምም አደርገዋለሁ፤ እጅግም አበዛዋለሁ፤ አሥራ ሁለት አለቆችንም ይወልዳል፥ ታላቅ ሕዝብም እንዲሆን አደርገዋለሁ።” (2)

“አዎ! እግዚአብሔር የባረከው እስማኤል የእኛ የአረቦች አባት ሆነ፡” አለ አህመድ፡
“ነገር ግን እኛ ሙስሊሞች እግዚአብሔር በይስሃቅ ዘሮች በኩል ብዙዎችን መልዕክተኞች እና ነቢያትም እንደላከ እናውቃለን።” ሀምዲ በመቀጠል” ይስሃቅ ኤሳውና ያዕቆብ የተባሉ ሁለት ወንዶች ልጆች ነበሩት። እግዚአብሔር ተስፋ የተደረገበት መሲሕ ከያዕቆብ እንደሚመጣ በሕልም በተገለጠለት ጊዜ እንዲህ ብሎትነበር፡-

“ እነሆም፥ እግዚአብሔር በላይ ቆሞበት ነበር፥ እንዲህም አለ፦ የአባትህ የአብርሃም አምላክ የይስሐቅም አምላክ እኔ እግዚአብሔር ነኝ፤ ይህችን አንተ የተኛህባትን ምድር ለአንተም ለዘርህም እሰጣለሁ፤
ዘርህም እንደ ምድር አሸዋ ይሆናል፤ እስከ ምዕራብና እስከ ምሥራቅ እስከ ሰሜንና እስከ ደቡብ ትስፋፋለህ፤ የምድርም አሕዛብ ሁሉ በአንተ በዘርህም ይባረካሉ።” (3)

“እግዚአብሔር ከያዕቆብ ጋር በተነጋገረ ጊዜ ለአብርሃም የገባውን ዋናውን የተስፋውን ቃል ብዙውን ክፍሎች መድገሙ የሚደንቅ ነው” አለ አህመድ።
“ይህ የሆነበት ምክኒያት ከአንድ ትውልድ ወደ ሌላው ትውልድ የሚተላለፍ ተመሳሳይ ተስፋ ስለሆነ ነው” አለ ሀምዲ። “ግን አህመድ፡ እንደምታየው እግዚአብሔር
የምድርን ሕዝቦች ሁሉ በያዕቆብ ልጅ በኩል መባረክ ነበረበት።” አለ።
“አዎ፡ እናም መሲሑ እንደገና የመጽሐፍ ቅዱስ ዋናው ፍሬ ሀሳብ (ጭብጥ) እንደሚሆን መጠርጠር ጀምሬያለሁ” ሲል አህመድ በፈገግታ መለሰ።
“ልክ ነህ” አለ ሃምዲ። “ከእስራኤል ልጆችም (ባኒ ኢስራኢል) ብዙ ቤተሰቦች ነበሩ። ጥያቄው እግዚአብሔር መሲሑ የሚመጣበትን ቤተሰብንም ገልጦ እንደሆነ ነው። እግዚአብሔር ዳዊትን (ሰይደና ዳዉድን) መርጦ ከእርሱም ጋር ቃል ኪዳን አደረገ። በብዙ ትንቢቶችም እግዚአብሔር መሲሑ ከነብዩ ዳዊት ቤተሰብ እንደሚማጣ አሳይቷል።

ከዳዊት ከሁለት መቶ ዓመታት በኋላ የነበረው ነብዩ ኢሳያስ የእሴይን ቤተሰብ ከዛፍ ግንድ ጋር አመሳስሎታል። የዳዊት አባት እሴይ ይባል ነበር። ከዚህ ቤተሰብ የጌታ መንፈስ የሚያርፍበት አንድ ሰው ይመጣል። ለምድር ድሆች ፍትሕን ያመጣል። እንደ ገነት የምትመስል
መንግስትን ይፈጥራል፡ በዚህች መንግስት ውስጥም ያሉ ሁሉ ጌታን ያውቃሉ። ኢሳያስ እንዲህ ሲል ጽፏል፡-

“ከእሴይ ግንድ በትር ይወጣል፥ ከሥሩም ቍጥቋጥ ያፈራል።
የእግዚአብሔር መንፈስ፥ የጥበብና የማስተዋል መንፈስ፥ የምክርና የኃይል መንፈስ፥ የእውቀትና እግዚአብሔርን የመፍራት መንፈስ ያርፍበታል…
ነገር ግን ለድሆች በጽድቅ ይፈርዳል፥ ለምድርም የዋሆች በቅንነት ይበይናል፤ በአፉም በትር ምድርን ይመታል፥ በከንፈሩም እስትንፋስ ክፉዎችን ይገድላል…
በዚያም ቀን እንዲህ ይሆናል፤ ለአሕዛብ ምልክት ሊሆን የቆመውን የእሴይን ሥር አሕዛብ ይፈልጉታል፤ ማረፊያውም የተከበረ ይሆናል…” (4)

”ይህን መብት እኔም እንዳገኘሁ እስኪ እንመልከት” አለ አህመድ።
“እግዚአብሔር መሲሑ የአብርሃም፣ የይስሃቅ፣ የያዕቆብ እና የዳዊት ልጅ መሆን እንዳለበት ገለጧል።”
“በትክክል!” ሀምዲ በፈገግታ መለሰ። “ወንጌልን ስናነብ መሲሑ በትንቢቶች መሰረት እንደተወለደ ማየት እንችላለን። ለዚህም ነው ወንጌሉ ሲጀምር በዘር ሐረግ የሚጀምረው። ይህም መሲሑ የአብርሃምና የዳዊት ልጅ መሆኑን በትክክል ያረጋገጣል።”
“የመጽሐፍ ቅዱስ ዋናው ፍሬ ሀሳብ ኢየሱስ የማሪያም ልጅ መሆኑን በድጋሚ አረጋግጧል” አለ አህመድ።” ግን ሀምዲ፡ “ተጨማሪ አስቸጋሪ ጥያቄዎች እንዳሉኝ እንደምታውቅ እርግጠኛ ነኝ። ግን ለቀጣዩ ጊዜ አስቀምጣቸዋለሁ።”
“አል-ሰላም አሌይኩም።”
“አሌይኩም አል-ሰላም”

እግዜብሔር አንድ ነው

“ምን ይታይሃል?” አለ አህመድ ሶስት ጣቶቹን ወደ ላይ አንስቶ።
“በአንዱ እጅህ ላይ ሶስት ጣቶችን አያለሁ” አለ ሀምዲ በፈገግታ፡ አህመድ ለማለት ያሰበውን እያወቀ። ”ሃምዲ፡” አህመድ ቀጠለ፡ እግዚአብሔር አንድ ነው ወይስ ሶስት ነው ብለህ ታምናለህ?”
”ምናልባት እኔ የማምንበት መንገድ ሙሉ በሙሉ ላይገባህ ይችላል” አለ ሀምዲ “ነገር ግን እኔ ሰማይን እና ምድርን በፈጠረ፣ ማንኛውንም ነገር ማድረግ በሚችል፣ ሁሉንም ነገር በሚያውቅ፣ እና በሁሉም ቦታ በሚገኝ በአንድ እውነተኛ አምላክ እንደማምን መረዳት አለብህ። እምነቴ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተመሰረተ መሆኑንና የእግዚአብሔርም ቃል እግዚአብሔር አንድ እንደሆነ እንደሚያስተምር ታውቃለህ። ይህ እውነት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በብዙ ቦታዎች ተጽፏል።”
“ግን እግዚአብሔር በአንድ ጊዜ ሦስት እና አንድ ሊሆን አይችልም” ሲል አህመድ አጥብቆ ተናገረ።
“እንደገና ሦስት ጣቶቹን አንስቶ” አንድ ሲደመር አንድ ሲደመር አንድ እኩል ይሆናል ሦስት እንጂ አንድ አይደለም” አለ።
“አንተ ስንት አህመድ ነህ?“ “አንድ ወይንስ ሁለት ነህ?” በማለት ሀምዲ ጠየቀ።
አህመድ “በእርግጥ አንድ ነኝ” ሲል መለሰ።
“እግዚአብሔር አንተን በአካል እና በመንፈስ ፈጥሮሃል” አለ ሀምዲ። ”የአንተ አካል አህመድ ነው?“ ሲል ሀምዲ ጠየቀ። “አዎ”
“ግን የአንተ መንፈስስ?” አህመድ ነውን?” ሲል ሀምዲ ጠየቀ።
“አዎ ልክ ነው” አለ አህመድ፡ ሀምዲ ቀጥሎ ምን ለማለት እንደፈለገ በመገንዘብ።
ሀምዲ ቀጠለ፡ ”እግዚአብሔር እኛን ሁለት በአንድ አድርጎ ከፈጠረን ለእርሱ በአንድ ሦስት መሆን የማይቻለው ለምንድ ነው?” ከአጭር ጊዜ ዝምታ በኋላ ሀምዲ፡ ”እግዚአብሔር ራሱን በሦስት አካላት የሚገልጥ ውስብስብ አንድነት ነው ማለት እንችላለን። ልጠይቅህ አህመድ፡ አንድ ጊዜ አንድ ጊዜ አንድ ስንት ነው?”
“አንድ” አለ አህመድ በቀስታ። “ነገር ግን ኢየሱስ የማሪያም ልጅ ሰው ብቻ እንጂ የእግዚአብሔር ልጅ አይደለም።” አህመድ ሀምዲን አትኩሮ እያየ “መሲሁ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ታምናለህ ሀምዲ?“
“አንተ ምን ብዬ የማምን ይመስልሃል?“ ሲል ሀምዲ ጠየቀ።
”በትክክል እርግጠኛ አይደለሁም” አለ አህመድ “ግን እግዜብሔር ከድንግል ማሪያም ጋር አካላዊ ግንኙነት እንዳደረገ እና አንድ ወንድ ልጅ ወልደዋል ብለህ ታምናለህ ብዬ አስባለሁ።”
“አስታግህፈር አላህ! (እግዚአብሔርን ይቅርታ እጠይቃለሁ) አለ ሀምዲ ድምጹን ጎላ አድርጎ።” እኔ በፍጹም እንደሱ አላምንም፡ የመሲሁ ተከታይ ሆኖ እንደሱ የሚያምንም ማንንም አላውቅም።”
“ታዲያ በምን ታምናለህ?“ ሲል አህመድ በመገረም ጠየቀ።
“እኔ እግዚአብሔር ዘላለማዊ እንደሆነ ማንኛውም ነገር ከመፈጠሩ በፊት እንደነበረ አምናለሁ” በማለት ሀምዲ ጀመረ። “ወንጌል ስለ መሲሑ ማንነት ሲያብራራ፡ ልክ ወደ እዚህ ዓለም ከመወለዱ ጋር አይጀምርም፡ ነገር ግን እግዚአብሔር ዓለምን ከመፍጠሩ በፊት በዘልአለማዊነት ይጀምራል። በወንጌልም እንዲህ ተብሎ ተጽፏል፡-

“በመጀመሪያው ቃል ነበረ፥ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፥ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ።

ይህ በመጀመሪያው በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ።
ሁሉ በእርሱ ሆነ፥ ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም።
በእርሱ ሕይወት ነበረች፥ ሕይወትም የሰው ብርሃን ነበረች።" (1)

"እግዚአብሔር ዓለምን በቃሉ ነው የፈጠረው:: አይደለም እንዴ?"
"አዎ ትክክል ነው። እግዚአብሔር "ይሁን!" አለ እናም ሆነም" (ኩን ፉ ያኩን)" ሲል መለሰ አህመድ።
"ስለዚህ እግዚአብሔር ዓለምን በቃሉ ነው የፈጠረው" አለ ሀምዲ። "ይህ ከእግዚአብሔር የወጣው ቃል የእግዚአብሔር አካል ነበር፤ በእግዚአብሔር የመፍጠር ኃይል እና በሁሉም ባሕሪያቱ የተሞላ ነበር። በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ሕይወት ነበረ፡ እና ቃሉ ባለበት ቦታ ሁሉ ሕይወት በተለያዩ መልኮች ተፈጠሩ።"
"አዎ እኔም በዚህ እስማማለሁ ግን 'ቃልም እግዜብሔር ነበር' የሚለው አገላለጽ በትክክል ምን ማለት ነው?" ሲል አህመድ ጠየቀ።
"እኔ በፍርድ ቤት ብመሰክር፡ እኔን ከቃሌ መለየት አትችልም" አለ ሀምዲ። "ቃሎቼ እኔን ስለሚወክሉ የእኔ የራሴ ይሆናሉ። "እኛ እዚህ ተቀምጠን ስንነጋገር ቃሎቻችን ስለሆኑ እኛ በቃሎቻችን እንወከላለን። እግዚአብሔር አጽናፈ ዓለሙን ሲፈጥር የተናገረው ቃል ከእርሱ ጋር አንድ ነበር። እግዚአብሔርን ከቃሉ መለየት አንችልም። ከእርሱ ጋር አንድ የሆነው እና ሁሉንም ባሕሪያቱን የያዘው ይህ ዘላለማዊ የእግዚአብሔር ቃል በማሪያም ልጅ በኢየሱስ ተገልጧል፡ እንዲህ ተብሎ እንደተፃፈ:-

"ቃልም ሥጋ ሆነ፤ ጸጋንና እውነትንም ተመልቶ በእኛ አደረ፥ አንድ ልጅም ከአባቱ ዘንድ እንዳለው ክብር የሆነው ክብሩን አየን።" (2)

"እግዚአብሔር ስለ ራሱ የተናገረው ሁሉ፡ ባሕሪያቱ ሁሉ በመሲሑ ውስጥ ተገልጧል። እግዚአብሔር ቅዱስ ነው። ሰዎች መሲሑ ምን ያህል ንጹሕ እንደሆነ ሲያዩ፡ የእግዚአብሔርን ቅድስና በእርሱ ውስጥ አዩ። እግዚአብሔ ፍቅር ነው። መሲሑ ሰዎችን እንዴት እንደወደደ ሲያዩ የእግዚአብሔርን ፍቅር በእርሱ ውስጥ አዩ። እግዚአብሔር ሁሉን ነገር ማድረግ ይችላል። እርሱ ሁሉን ቻይ ነው። ሰዎች መሲሑ በውኃ ላይ እንዴት እንደተራመደ ፣ ሞገዱን እንዴት እንደተናገረ፣ ነፋሱን እና ማዕበሉን እንዴት ፀጥ እንዳሰኘ፡ እንዴት እንጀራ እንደፈጠረ፣ ዓይነ ስውራንን እንዴት እንደፈወሰ እና ሙታንን እንዳስነሳ ሲያዩ፡ የእግዚአብሔርን ኃይልና ክብር በእርሱ እንደተገለጠ አዩ።"
"ግን በሁሉም ስፍራ የሚገኘው እግዚአብሔር በሰው ልጅ እንዴት ሊገደብ ይችላል?" አለ አህመድ በመቀጠል። "እግዚአብሔር በመሲሁ ውስጥ በነበረበት ጊዜ አጽናፈ ዓለሙን ረስቶት ነበር ማለት ነው? "
"አህመድ" አለ ሀምዲ፡ "እንበልና፡ ማለቂያ በሌለው ውቂያኖስ ላይ ብንወጣና እና ብርጭቆውን ውሃ ብንሞላው እና ውሃውን ብንመረምረው ልክ በውቂያኖስ ውስጥ ካለው ውሃ ጋር ተመሳሳይ ሆኖ እናገኘዋለን።
ከመሲሑም ጋር ተመሳሳይ ነው። ዘልአለማዊ፡ ሁሉን ቻይ የሆነው እግዚአብሔር በሁሉም ቦታ አለ። በተመሳሳይ ጊዜ በመሲሑ ውስጥ በተመሳሳይ ባሕሪያት እና ኃይል እራሱን ይገልጣል። ነገር ግን እግዚአብሔር በመሲሑ ውስጥ እራሱን ስለገጠ የተወሰነ አይደለም። አሁንም እሱ ማለቂያ የለውም።"

“ግን እግዜብሔር እራሱን በሰው ውስጥ ሊገልጥ አይችልም” አለ አህመድ። እግዚአብሔርን እንዴት እንወስነዋለን?“ ሲል ሀምዲ ጠየቀ። “ሁሉን ቻይ የሆነው እግዚአብሔር እንዴት አይችልም እንላለን? ሁሉንም ማድረግ አይችልም?”
“አዎ ሁሉንም ማድረግ ይችላል” ሲል አህመድ መለሰ፡ ”ግን ራሱን በሰው ልጅ ውስጥ ገልጧል ብዬ ማመን አልችልም።” “ግን ይህ ችግር ሊሆን የሚችለው ለእኛ እንጂ የፈለገውን ሁሉ ማድረግ ለሚችለው ለእግዚአብሔር እንዳልሆነ መስማማታችን ጥሩ ነው” አለ ሀምዲ።
“ታሪኩን አስቀድመህ የማታውቅ ቢሆን እና፡ አንድ ሰው እግዚአብሔር በሚቃጠል ቁጥቋጦ ውስጥ ራሱን እንደገለጠ እና ከዚያ ቁጥቋጦ ውስጥ ሙሴን እንደተናገረው ቢነግርህ ምን ትል ነበር?”
አህመድ ለጥቂት ጊዜ አሰበ እና፡ እግዚአብሔር ራሱን ከቁጥቋጦ ውስጥ ከመግለጥ የበለጠ ከባድ ሊሆን እንደማይችል ሲረዳ ለራሱ ፈገግ አለ።
ሀምዲ ቀጠለ፡ “አህመድ ትንሽ አስብ፡ ‘የእግዚአብሔር ቃል’ እና ‘የእግዚአብሔር መንፈስ’ (ካሊማት አላህ ዋ ሩህ አላህ) የተባለው አካል በእርግጥ ማነው? “የእግዚአብሔር መንፈስም ከእግዚአብሔር ጋር አንድ ነው። የእግዚአብሔር መንፈስ ድንግል ማሪያምን እንደሸፈናት እና እንደፀነሰች ከዛም መልአኩ ገብርኤልም እንደተናገራትና መሲሑን እንደወለደች እናውቃለን፡-

“መልአኩም መልሶ እንዲህ አላት፡- መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል፥ የልዑልም ኃይል ይጸልልሻል ስለዚህ ደግሞ ከአንቺ የሚወለደው ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል።” (3)

“አሁን ጥያቄው በዚህ መንገድ ወደ እዚህ ዓለም የመጣው ማነው የሚለው ነው። አህመድ፡ በመሲሑ ዘመን አንተ ዶክተር ብትሆን እና የልደት የምስክር ወረቀት የመጻፍ ኃላፊነት የአንተ ቢሆን ኖሮ ምን ብለህ ትጽፍ ነበር? ስሙስ ማን ነበር?“
“የማሪያም ልጅ ኢየሱስ ብዬ እጽፍ ነበር ብዬ አስባለሁ” አለ አህመድ።
“የእናቱን ስም?”
“አዎ እሱም ድንግል ማሪያም ይሆን ነበር” አለ አህመድ።
”ከዚያም ወደ አባቱ ስም እንምጣ” አለ ሀምዲ በፈገግታ።
”አባት አልነበረውም” ሲል አህመድ በፈገግታ መለሰ።
“በእርግጥ ምድራዊ አባት ስላልነበረው ያንን መስመር ክፍቱን መተው እንችላለን” አለ ሀምዲ። “--ወይም “የእግዚአብሔር ቃል” እና “የእግዚአብሔር መንፈስ” የተባለው መነሻው ምንድን ነው? ከሰማይ የወረደው የተባለው ማንነቱ ምንድን ነው?” ብለን ራሳችንን መጠየቅ እንችላለን።
እርሱ ራሱ እንዲህ ብሏል፡-

“ የእግዚአብሔር እንጀራ ከሰማይ የሚወርድ ለዓለምም ሕይወትን የሚሰጥ ነውና አላቸው። …
ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፡- የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ፤ ወደ እኔ የሚመጣ ከቶ አይራብም በእኔ የሚያምንም ሁልጊዜ ከቶ አይጠማም። (4)

---ከሰማይ የወረደ ሕያው እንጀራ እኔ ነኝ፤ ሰው ከዚህ እንጀራ ቢበላ ለዘላለም ይኖራል፤ እኔም ስለ ዓለም ሕይወት የምሰጠው እንጀራ ሥጋዬ ነው።” (5)

“አህመድ፡ እርሱ እራሱን ለሰው ልጆች ሁሉ መሥዋዕት አድርጎ ለማቅረብ ሲል መጣ። ምድራዊ እንጀራን የሚበላ አካላዊ ሕይወትን ይቀበላል፡ ከሰማይ የወረደውን የእግዚአብሔርን እንጀራ የሚበላ ሁሉ ግን መንፈሳዊ ሕይወትን፡የዘላለም ሕይወትን ይቀበላል። በመሲሑ የሚያምን እና ከእርሱ የሚካፈል ሁሉ ለእግዚአብሔር ያለውን ውስጣዊ ረሃብና ጥማትን የሚያረካ ሕይወትን ያገኛል። እኔም ራሴ የተለማመድኩት ይህንኑ ነው። መሲሑ ከእግዚአብሔር ለአንተ የተሰጠ ስጦታ ነው፡ አህመድ።“
“እኔ ገና እስካሁን ለእርሱ ዝግጁ አይደለሁም።” አለ አህመድ በዝግታ። “ብዙ ሀሳቦች በአእምሮዬ እየተመላለሱ ነው። እኔ አሁን አንተ በእግዚአብሔር የምታምንበትን መንገድ ሙሉ በሙሉ በተሳሳተ መንገድ እንደተረዳሁህ አሁን አወቅሁ። አንተ በአንድ እውነተኛ አምላክ እንደምታምንና እርሱም ራሱን በመሲሑ ውስጥ እንደገለጠ ቀስ በቀስ መረዳት ጀምሬያለሁ።
መሲሑን በሙሉ ልቤ እንደምወደው ታውቃለህ፡ ነገር ግን አሁንም መልስ የሚያስፈልጋቸው በርካታ ጥያቄዎች አሉኝ።
ግን በሚቀጥለው ጊዜ ስለእነሱ ማውራት እንችላለን ። አንችልም ሀምዲ?”
“መልሱን በጉጉት እጠብቃለሁ” ሲል መለሰ ሀምዲ።
“አል-ሰላሙ አሌይኩም።”
“አሌይኩም አል-ሰላም።”

እግዚአብሔር እና ሰው

“ባለፈው የመጨረሻው ውይይታችን ቀንና ለሊት ማለት ይቻላል እያስብኩ ነበር”
“አንተ በመጀመሪያ ኢየሱስ የማርያም ልጅ ሰው ነው አልከኝ። ቀጥሎ እግዚአብሔር ራሱን በእርሱ ውስጥ ገለጠ አልከኝ። በእርግጥ እርሱ ማን እንደሆነ ማወቅ እፈልጋለሁ። መሲሑ የማርያም ልጅ ብቻ ሆኖ ሳለ አንተ ግን የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ አድርገህ ማቅረብህ እውነት አይደለምን?”
አለ አህመድ።
“አህመድ” በማለት ጀመረ ሀምዲ ”ለዚህ ጥያቄ መልሱ ከእግዚአብሔር ጋር ለሚኖረን የዘላለም ሕይወት፡ በእዚህ ምድር ሆነ፡ ለአሁን እና ለዘላለሙ የሚሆን ዋናው ቁልፍ ነው። ሰውን ከእግዚአብሔር ጋር እኩል አድርገን ከቆጠርን (አንድን ሰው ከእግዚአብሔር ጋር በተመሳሳይ ደረጃ ላይ ማስቀመጥ) ”ሽሪክ” ይሆናል ማለት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስተምረው ግን እግዜብሔር እራሱን በሰው ውስጥ እንደገለጠ እንጂ በሌላ መንገድ አልገለጠም። መሲሁ ሰው ሆኖ መወለዱን ሁለታችንም እንስማማለን።
እንደ ነቢያቶች መሰረት እሱ የኢብራሂም ልጅ ነው፡ የዳዊት ልጅ እና የማሪያም ልጅ ነው። ነገር ግን ከመሲሑ መወለድ ከረጅም ጊዜ በፊት በተሰጡት ትንቢቶች ውስጥ፡ እግዚአብሔር በመሲሑ በኩል ወደ እኛ እንደሚመጣ ያስተምረናል።”
“ከመሲሑ በፊት የነበሩት ሐዋሪያትና ነቢያት እግዚአብሔር ራሱን በመሲሁ ውስጥ እንደሚገልጥ አስቀድመው ተናግረው ነበር ማለትህ ነው?” ሲል አህመድ በመገረም ጠየቀ።
“የመጽሐፍ ቅዱስ ዋናው ጭብጥ (ፍሬ-ሀሳብ) መሲሑ ነው፡ ስለዚህ እግዚአብሔር ስለ መሲሑ ያለውን እውነት በነቢያት በኩል መግለጡ ሊያስደንቀን አይገባም” አለ ሀምዲ።
አህመድም ”እስቲ አሳየኝ” እኔ ለማወቅ በጣም ፍላጎት አለኝ“ ሲል በትህትና ጠየቀ።
ሀምዲ ከመናገሩ በፊት ለጥቂት ጊዜ አሰበና “እግዚአብሔር ከ.ክ.ል.ደት ከ 700 ዓመታት በፊት መሲሑ በቤተልሔም ከተማ እንደሚወለድ እንዲሁም ይህ የሚወለደው ከመወለዱ ከረጅም ጊዜ በፊት የነበረ እንደነበረም ለነብዩ ሚኪያስ ገለጾለት ነበር፡-

“አንቺም ቤተ ልሔም ኤፍራታ ሆይ፥ አንቺ በይሁዳ አእላፋት መካከል ትሆኚ ዘንድ ታናሽ ነሽ፤ ከአንቺ ግን አወጣጡ ከቀድሞ ጀምሮ ከዘላለም የሆነ፥ በእስራኤልም ላይ ገዥ የሚሆን ይወጣልኛል።” (1)

“በወንጌል እንደተፃፈው መሲሑ በእርግጥም በቤተልሔም ከተማ ተወለደ፡-”

“ዮሴፍም ደግሞ ከዳዊት ቤትና ወገን ስለ ነበረ ከገሊላ ከናዝሬት ከተማ ተነሥቶ ቤተ ልሔም ወደምትባል ወደ ዳዊት ከተማ ወደ ይሁዳ፥ ፀንሳ ከነበረች ከእጮኛው ከማርያም ጋር ይጻፍ ዘንድ ወጣ።
የበኩር ልጅዋንም ወለደች፥ በመጠቅለያም ጠቀለለችው፤ በእንግዶችም ማደሪያ ስፍራ ስላልነበራቸው በግርግም አስተኛችው። (2)
“አሁን ጥያቄው መሆን ያለበት ወደ እዚህ ዓለም ከመወለዱ ከረጅም ጊዜ በፊት የነበረው እርሱ ማን ነው የሚለው ነው።”

እርሱ ራሱ በኢየሩሳሌም (በአል-ቁድስ) ከአንዳንድ ከተበሳጩ አይሁዶች ጋር ባደረገው ውይይት ላይ ምን እንዳላቸው እናያለን፡-

“አባታችሁ አብርሃም ቀኔን ያይ ዘንድ ሐሤት አደረገ፥ አየም ደስም አለው።
57 አይሁድም፦ ገና አምሳ ዓመት ያልሆነህ አብርሃምን አይተሃልን? አሉት።
ኢየሱስም፦ እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ አብርሃም ሳይወለድ እኔ አለሁ አላቸው።” (3)

“አብርሃም ከ 2000 ዓመት ቅድመ ልደተ ክርስቶስ በፊት እንደነበረ እናውቃለን።”
“ስለዚህ መሲሑም ራሱ ከመወለዱ በፊት እንደነበረ ተናግሯል” አለ አህመድ።
“ነገር ግን እግዚአብሔር እራሱን በመሲሑ ውስጥ እንደሚገልጥ የተጠቀሰው በየትኛው የነቢያት ክፍል ነው? “ይህ በብዙ ቦታዎች ተጽፏል” አለ ሀምዲ።
“ነቢዩ ኢሳይያስ የማሪያም ልጅ ኢየሱስ ካደገበት ትንሽ መንደር ስለሚመጣ ሰው ይናገራል።”በእግዚአብሄር ሰላም የሚገለጽ እንደ እግዚአብሔር ባህሪያት ያለ ዘልአለማዊ መንግስት ይፈጥራል። የዳዊት ልጅ የሆነውም እርሱ ራሱ በዚህ መንግስት ለዘልአለም ይነግሣል። ነብዩ የመሲሑን ባህሪያት በተሰጡት የተለያዩ ስሞች ይገልፃል፡-

“ሕፃን ተወልዶልናልና፥ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና፤ አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል፤ ስሙም ድንቅ መካር፥ ኃያል አምላክ፥ የዘላለም አባት፥ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል።
ከዛሬ ጀምሮ እስከ ዘላለም ድረስ በፍርድና በጽድቅ ያጸናውና ይደግፈው ዘንድ በዳዊት ዙፋንና በመንግሥቱ ላይ አለቅነቱ ይበዛል፥ ለሰላሙም ፍፃሜ የለውም። የእግዚአብሔር ቅንዓት ይህን ያደርጋል።” (4)

“እግዚአብሔር ለአንድ ሰው የሚሰጠው ስም የዚያን ሰው ባህሪያት እንደሚገልጹ እናውቃለን።” ስለዚህ ማነው እሱ” “ድንቅ አማካሪ”፣ “ኃያል አምላክ”፣ “የዘልአለም አባት”፣ እና “የሰላም አለቃ” የሚሉት ስሞች የተሰጡት ለማን ነው?” አህመድ።
”ይህ ከመወለዱ በፊት ነቢያት የሳሉት የመሲሑ ስዕል ለእኔ ቅርጽ መያዝ ጀምሯል” አለ አህመድ፡ “ግን እግዚአብሔር ራሱ ወደ ፈጠረው ዓለም እንደሚመጣ በእርግጥ ይናገራል?” አለ።
“መጥምቁ ዮሐንስ (ያህያ ኢብኑ ዘካሪያስ) ከመሲሑ ጋር በተመሳሳይ ጊዜ ኖሯል” አለ ሀምዲ። “ሰዎች ንስሐ እንዲገቡ እና በእርሱ እንዲያምኑ፣ ለመሲሑ መንገድ እንዲያዘጋጅ ከእግዚአብሔር የተላከ ነበር። ዮሐንስ ራሱ ማን እንደሆነ እና እግዚአብሔር ለምን እንደላከው ሲጠየቅ፡ ከነቢዩ ኢሳያስ ከምዕራፍ 40 የተፃፈውን በመጥቀስ እንዲህ አለ ፡-

“የአዋጅ ነጋሪ ቃል፦ የእግዚአብሔርን መንገድ በምድረ በዳ ጥረጉ፥ ለአምላካችንም ጐዳና በበረሀ አስተካክሉ።
ሸለቆው ሁሉ ከፍ ይላል፥ ተራራውና ኮረብታውም ሁሉ ዝቅ ይላል፤ ጠማማውም ይቃናል፥ ስርጓጉጡም ሜዳ ይሆናል፤

የእግዚአብሔርም ክብር ይገለጣል፥ ሥጋ ለባሹም ሁሉ በአንድነት ያየዋል፥ የእግዚአብሔር አፍ ይህን ተናግሮአልና።” (5)

“ከነቢዩ ኢሳያስ የተወሰደው ሥዕል የአንድ ታላቅ ንጉሥ ጉብኝትን ይገልፃል። ሰዎች በምድረ በዳ ውስጥ አዲስ እና ቀጥ ያለ አውራ ጎዳና ሊሰሩለት ነበር። ግን ይህ እንግዳ ንጉሥ ማነው አህመድ?”
“መልካም እንደ ነቢዩ ገለጻ፡ እርሱ ጌታ አምላካችን ነው” አለ አህመድ በጸጥታ።
ሀምዲ በመቀጠል” በተመሳሳይ ክፍሉን የበለጠ ስናነብ ሥዕሉ ይበልጥ ግልጽ ይሆናል፡-

“የምስራች የምትነግሪ ጽዮን ሆይ፥ ከፍ ወዳለው ተራራ ውጪ፤ የምስራች የምትነግሪ ኢየሩሳሌም ሆይ፥ ድምፅሽን በኃይል አንሺ፤ አንሺ፥ አትፍሪ፤ ለይሁዳም ከተሞች፡- እነሆ፥ አምላካችሁ! ብለሽ ንገሪ።
እነሆ፥ ጌታ እግዚአብሔር እንደ ኃያል ይመጣል ክንዱም ስለ እርሱ ይገዛል፤ እነሆ፥ ዋጋው ከእርሱ ጋር ደመወዙም በፊቱ ነው።
መንጋውን እንደ እረኛ ያሰማራል፥ ጠቦቶቹን በክንዱ ሰብስቦ በብብቱ ይሸከማል፥ የሚያጠቡትንም በቀስታ ይመራል።”. (6)

“መሲሑን በእርግጥም ለሚያምኑ ሁሉ እረኛ ሆኖ መጣ።” እርሱም ራሱ እንዲህ ብሏል፡-

“**መልካም እረኛ እኔ ነኝ። መልካም እረኛ ነፍሱን ስለ በጎቹ ያኖራል።”** (7)

“ግን አህመድ፡ እንደ ነቢዩ አባባል እረኛ ሆኖ የሚመጣው ማነው?“ ጌታ እግዚአብሔር ራሱ እንደሆነ መገለጹን መቀበል አለብኝ” ሲል አህመድ መለሰ፡ አሁን በነብዩ ቃል በደንብ ተናወጠ።
ሀምዲ ቀጠለ፡ አህመድ አንተ እንደተረዳኸው፡ ስለ መሲሑ የተነገሩት ትንቢቶች ሁሉ በመርያም ልጅ በኢየሱስ ላይ ነው የተፈፀሙት። መሲሑ ከመወለዱ በፊት መልአኩ ገብርኤል ወደ መጥምቁ ዮሐንስ የወደፊት አባት ወደ ዘካሪያስ መጥቶ መልአኩ ለዘካሪያስ ወንድ ልጅ እንደሚወልድ እና ልጁም ምን ዓይነት ልዩ ተግባር እንደሚኖረው ነገረው። መልአኩ ገብርኤል እንዲህ አለ፡-

“**በጌታ ፊት ታላቅ ይሆናልና፥ የወይን ጠጅና የሚያሰክር መጠጥ አይጠጣም፤ ገናም በእናቱ ማኅፀን ሳለ መንፈስ ቅዱስ ይሞላበታል፤**
ከእስራኤልም ልጆች ብዙዎችን ወደ ጌታ ወደ አምላካቸው ይመልሳል።
እርሱም የተዘጋጁትን ሕዝብ ለጌታ እንዲያሰናዳ፥ የአባቶችን ልብ ወደ ልጆች የማይታዘዙትንም ወደ ጻድቃን ጥበብ ይመልስ ዘንድ በኤልያስ መንፈስና ኃይል በፊቱ ይሄዳል።” (8)

“እንደ ወንጌል ከሆነ መጥምቁ ዮሐንስ ማንን ይቀድማል፡አህመድ?” እግዚአብሔር አምላካቸው” ሲል አህመድ መለሰ።
ሀምዲ በመቀጠል” መጥምቁ ዮሐንስ ገና አዲስ የተወለደ ልጅ በነበረበት ጊዜ “ዘካሪያስ” አዲስ በተወለደው ልጁ ላይ ትንቢት ተናገረ፡-

“ደግሞም አንተ ሕፃን ሆይ፥ የልዑል ነቢይ ትባላለህ፥ መንገዱን ልትጠርግ በጌታ ፊት ትሄዳለህና፤
እንደዚህም የኃጢአታቸው ስርየት የሆነውን የመዳን እውቀት ለሕዝቡ ትሰጣለህ፤
78 ይህም ከላይ የመጣ ብርሃን በጐበኘበት በአምላካችን ምሕረትና ርኅራኄ ምክንያት ነው፤”. (9)

“አህመድ ያህያ ኢብን ዘካሪያስ እንደ ነቢዩ ኢሳያስ: እንደ መልአኩ ገብርኤል እና እንደ አባቱ ዘካሪያስ ቃል በእግዚአብሔር ፊት መሄድ እንደ ነበረባቸው እንዲሁም ይህ የሚመጣው እግዚአብሔር ራሱ መሆኑን አየህ?“
“አዎ! ይህንን ማየት እችላለሁ” እናም ይህ ሁሉ መሲሑ በእርግጥ በመጣ ጊዜ ተረጋግጧል ብዬ መገመት እችላለሁ” አለ አህመድ በቁም ነገር።
“አዎ በዝርዝር” አለ ሀምዲ። ድንግል ማሪያም በዳዊት ከተማ በቤተልሔም መሲሑን በወለደች ጊዜ የጌታ መልአክ ከከተማይቱ ውጭ ላሉት አንዳንድ እረኞች ተገልጾ እንዲህ አላቸው:-

“መልአኩም እንዲህ አላቸው፦ እነሆ፥ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ፤
ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኃኒት እርሱም ክርስቶስ ጌታ የሆነ ተወልዶላችኋልና።” (10)

“መሲሑ እራሱ ጌታ መሆኑ በወንጌል ውስጥ በተደጋጋሚ ተረጋግጧል።” እሱም ራሱ እንዲህ ብሏል፦

“እኔና አብ አንድ ነን።” (11)

አህመድ እንዲህ አለ፣-”አስቀድሜ ለማርያም ልጅ ለኢየሱስ ታላቅ ፍቅርና አክብሮት ነበረኝ” አለ አህመድ፡ “አሁን ግን ለመጀመሪያ ጊዜ መሲሑ ማን እንደሆነ እና ለምን በዓለም ውስጥ እንደ ተወለደ ሙሉውን ምስል ማየት እንደምችል አስባለሁ። ይህንን ለማስረዳት ጊዜህን ሰጥተህ ጥረት ስላደረግህ ከልቤ አመሰግንሃለሁ ሀምዲ።“
“አህመድ” አለ ሀምዲ በቁም ነገር: “በመሲሑ በማመን እግዚአብሔር ለሁሉም ነገር ይቅርታን እና የዘልአለም ህይወትን ይሰጣል። ሞትን ድል የነሳው እና ሙታንን ያስነሳው መሲሑ እንዲህ ይላል፦

“ኢየሱስም፦ ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ፤ የሚያምንብኝ ቢሞት እንኳ ሕያው ይሆናል፤
ሕያው የሆነም የሚያምንብኝም ሁሉ ለዘላለም አይሞትም፤ ይህን ታምኚያለሽን? አላት።” (12)

“አህመድ፤ በመሲሑ እምነት የእግዚአብሔርን ስጦታ መቀበል ትፈልጋለህ?”
“አዎ አሁን ቆሞ በሬን የሚያንኳኳ ሆኖ ይሰማኛል” አለ አህመድ ዓይኖቹ እንባ እያቀረረሩ።
“የእግዚአብሔርን ስጦታ እንዴት መቀበል እችላለሁ?”
”አስቸጋሪ አይደለም” አለ ሀምዲ። በገዛ አንደበትህ ወደ እግዚአብሔር ጸልይ። ሁሉንም ነገር ተናዘዝ፡እግዚአብሔር ስለ እኛ ሁሉንም ነገር ያውቃል። በመሲሑ ስለ አንተ በተከፈለው መስዋዕትነት ይቅርታን ተቀበል። እግዚአብሔር በመንፈሱ ወደ ሕይወትህ ውስጥ እንዲገባ መሲሑን እንደ ደቀ

መዝሙሩ እንድትከተል ኃይል እንዲሰጥህ ጸልይ። ይህንን ፀሎት በመሲሑ ስም ጸልይ። እርሱ በመስዋዕቱ በአንተና በእግዚአብሔር አብ መካከል አስታራቂ ነው።" መሲሑን በዚህ መንገድ በእምነት እንደ እግዚአብሔር ስጦታ ስትቀበል፥ በሕይወትህ ውስጥ ተአምር ይከሰታል። መጽሐፍ ቅዱስ ዳግመኛ እንደተወለድክ ይናገራል። ከእግዚአብሔር አዲስ ሕይወት ታገኛለህ። በመሲሑ አማካኝነት ከእግዚአብሔር ጋር አዲስ የሆነ የግል ግንኙነት ውስጥ ትገባለህ። በወንጌል እንደተጻፈ እግዚአብሔር አባትህ አንተም ለእርሱ ልጅ ትሆናለህ፡ በወንጌልም መሲሑን ለተቀበሉት ሁሉ እንዲህ ተብሎ እንደተፃፈው፡-

"ለተቀበሉት ሁሉ ግን፥ በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው፤ (13)

አብረው ፀልየው ጌታን ካመሰገኑ በኋላ ሀምዲ በታላቅ ፈገግታ "ወደ ቤተሰቡ እንኳን በደህና መጣህ! አሁን በመሲሑ አማካኝነት በእግዚአብሔር ታላቅ ቤተሰብ ውስጥ ወንድማማቾች ነን።"
"እንዴት አድርጌ ላመስግንህ?" አለ አህመድ በደስታ ተሞልቶ። "እግዚአብሔርን አመስግን በዕየለቱም አድርገው።" ሲል መለሰ ሀምዲ። "እንደ አንተ በተመሳሳይ መንገድ መሲሁን የሚከተሉ ሌሎችን ፈልገህ ህብረት አድርግ። አሁን መሲሑ ደቀመዛሙርቱን እንዲጸልዩ ያስተማራቸውን ጸሎት በእውነት መጸለይ ትችላለህ፡-

"እንግዲህ እናንተስ እንዲህ ጸልዩ፡- በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ፥
ስምህ ይቀደስ፤ መንግሥትህ ትምጣ፤ ፈቃድህ በሰማይ እንደ ሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን፤
የዕለት እንጀራችንን ዛሬ ስጠን፤
እኛም ደግሞ የበደሉንን ይቅር እንደምንል በደላችንን ይቅር በለን፤
ከክፉም አድነን እንጂ ወደ ፈተና አታግባን፤ መንግሥት ያንተ ናትና ኃይልም ክብርም ለዘለዓለሙ፤
አሜን።" (14)

አባሪ

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች
አዲስ ዓለም አቀፍ ትርጉም (NIV)

የእግዚአብሔር በግ	**እግዜብሔር አንድ ነው**
1. ሮሜ 6፥23 2. ዮሐንስ 1፥29 3. ራዕይ 3፥20 **የእግዚአብሔር መስዋዕት** 1. ነኛ ጢሞቲዎስ 2፥5-6 2. ዕብራውያን 9፥22 3. ኢሳያስ 53፥4-7 4. መዝሙር 22፥14-18 5. ማርቆስ 10፥45 **ኃጢአት** 1. ዘፍጥረት 2፥16-17 2. ሮሜ 5፥12 3. ዘፍጥረት 3፥15 **የአብርሃም ልጅ** 1. ዘፍጥረት 12፥1-3 2. ዘፍጥረት 17፥19-21 3. ዘፍጥረት 28፥13-14 4. ኢሳያስ 11፥1,2,4,10	1. ዮሐንስ 1፥1-4 2. ዮሐንስ 1፥14 3. ሉቃስ 1፥35 4. ዮሐንስ 6፥33, 35 5. ዮሐንስ 6፥51 እግዚአብሔር እና ሰው 1. ሚክያስ 5፥2 2. ሉቃስ 2፥4-7 3. ዮሐንስ 8፥56-58 4. ኢሳያስ 9፥6-7 5. ኢሳያስ 40፥3-5 6. ኢሳያስ 40፥9-11 7. ዮሐንስ 10፥11 8. ሉቃስ 1፥17 9. ሉቃስ 1፥76-78 10. ሉቃስ 2፥10 11. ዮሐንስ 10፥30 12. ዮሐንስ 11፥25-26 13. ዮሐንስ 1፥12 14. ማቴዎስ 6፥9-13